የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፷፪
አዲስ አበባ ሐምሌ ፫ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

21st Year No.62
ADDIS ABABA 10th July, 2015

ማውጫ

አዋጅ ፱፻፰/፪ሺ፯ ዓ.ም

የግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ (ማሻሻያ) አዋጅ ........................................ገጽ ፰ሺ፪፻፺፬

CONTENTS

Proclamation No. 908/2015

Private Organization Employees' Pension (Amendment) Proclamation........................................Page 8294

## አዋጅ ቁጥር ፱፻፰/፪ሺ፯

## የግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁጥር ፯፻፲፭/፪ሺ፫ን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ (ማሻሻያ)አዋጅ ቁጥር ፱፻፰/፪ሺ፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ማሻሻያ

የግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁጥር ፯፻፲፭/፪ሺ፫ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-

## PROCLAMATION No. 908/20015

## A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE AMENDMENT OF PRIVATE ORGANIZATION EMPLOYEES' PENSION PROCLAMATION

WHEREAS it has become necessary to amend the Private Organization Employees' Pension Proclamation No. 715/2011;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

### 1. Short title

This Proclamation may be cited as the "Private Organization Employees' Pension (Amendment) Proclamation No.908/2015".

### 2. Amendment

The Private Organization Employees' Pension Proclamation No. 715/2011 is hereby amended as follows:

ያንዱ ዋጋ Unit Price 6.45

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩ Negarit G. P.O.Box 80001

፩/ የአዋጁ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጾች (፩) እና (፯) ተሠርዘው በሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጾች (፩) እና (፯) ተተክተዋል፡-

"፩/ 'የግል ድርጅት ሠራተኛ' ማለት በግል ድርጅት ውስጥ ከአርባ አምስት ቀናት ላላነሰ ጊዜ ደመወዝ እየተከፈለው ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ ወይም የተወሰነ ስራ ለመስራት የተቀጠረ ሰራተኛ ሲሆን የስራ መሪንም ይጨምራል። ሆኖም ለጥጥ ለቀማ፣ለሸንኮራ አገዳ ቆረጣ እና ሌላ መሰል በየዓመቱ ለተወሰነ ጊዜ ብቻ እየተደጋገመ የሚከናወን ስራን ለመስራት የተቀጠረ ሰራተኛን አያካትትም፤

፯/ 'አበል' ማለት የአገልግሎት ጡረታ አበል፣ የጤና ጉድለት ጡረታ አበል፣ የጉዳት ጡረታ አበል ወይም የተተኪዎች ጡረታ አበል ሲሆን የዳረጎት አበልን ይጨምራል፤"

፪/ በአዋጁ ከአንቀጽ ፲፩ ንዑስ አንቀጽ (፲፪) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፲፫) ተጨምሯል:-

"፲፫/በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተሰበሰበውን የጡረታ መዋጮ በ፴ ቀን ውስጥ ገቢ ያላደረገ የግል ድርጅት ገቢ ባልተደረገው የጡረታ መዋጮ ላይ ደመወዝ ከተከፈለበት ወር ቀጥሎ ካለው ወር የመጀመሪያ ቀን ጀምሮ በባንክ ማስቀመጫ ወለድ መጠን መሰረት የሚታሰብ ወለድ እና ፭ በመቶ ቅጣት ጨምሮ የመክፈል ግዴታ ይኖርበታል።"

፫/ የአዋጁ አንቀጽ ፲፮ ንዑስ አንቀጽ (፫) ፊደል ተራ (መ) ተሠርዞ ነባሩ ፊደል ተራ (ሠ) ፊደል ተራ (መ) ሆኖ ተሸጋሽጓል፤

1/ sub-articles (1) and (7) of Article 2 of the Proclamation are deleted and replaced by the following new sub-articles (1) and (7):

"1/ 'private organization employee' means a salaried person employed in a private organization for not less than forty five days for definite or indefinite period of time or piece of work including managerial employees. However it does not include employees engaged in cotton collection, sugar cane cutting and such other similar works regularly repeated in the course of the year;

7/ 'benefit' means retirement pension, invalidity pension, incapacity pension or survivors' pension and includes gratuity;"

2/ the following new sub-article (13) is added after sub-article (12) of Article 11 of the Proclamation:

"13/ If the private organization fails to pay pension contribution collected pursuant to sub article (1) of this Article within 30 days, it shall be liable to pay interest with the bank deposit interest rate including 5% penalty for the unpaid pension contribution calculated from the first day of the month following the last day of the month in which payment of salary has been effected.''

3/ paragraph (d) of sub-article (3) of Article 16 of the Proclamation is deleted and the existing paragraph (e) is restructured as paragraph (d);

፬/ የአዋጁ አንቀጽ ፲፮ ንዑስ አንቀጽ (፮) ተሠርዞ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጾች (፮) እና (፯) ከንዑስ አንቀጽ (፭) ቀጥሎ ተጨምረው ነባሩ ንዑስ አንቀጽ (፯) ንዑስ አንቀጽ (፰) ሆኖ ተሸጋሽጓል፡-

"፮/ በዚህ አዋጅ ወይም በመንግስት ሰራተኞች ጡረታ አዋጅ መሰረት የአገልግሎት ወይም የጤና ጉድለት ዳረጎት ተከፍሎት የሥራ ውሉ የተቋረጠ ሰራተኛ እንደገና በግል ድርጅት ሰራተኞች ጡረታ ዐቅድ በተሸፈነ የግል ድርጅት የተቀጠረ ከሆነ እና የወሰደውን ዳረጎት መልሶ ገቢ ካደረገ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፭ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የቀድሞ አገልግሎቱ ይታሰብለታል።

፯/ ይህ አዋጅ ከመውጣቱ አስቀድሞ በዚህ አዋጅ ወይም በመንግስት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ መሰረት የጡረታ መዋጮ ተመላሽ ተደርጎለት የነበረ ሰው እንደገና በግል ድርጅት ሰራተኞች ጡረታ ዐቅድ በተሸፈነ የግል ድርጅት ውስጥ ከተቀጠረ እና መጦሪያ ዕድሜ ላይ ከመድረሱ አስቀድሞ የወሰደውን መዋጮ ከባንክ የማስቀመጫ ወለድ ጭምር ተመላሽ ካደረገ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፭ ንዑስ አንቀጽ (፫) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የቀድሞ አገልግሎቱ ይታሰብለታል።"

፭/ የአዋጁ አንቀጽ ፲፰ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተተክቷል፡-

4/ sub-article (6) of Article 16 of the Proclamation is deleted and the following new sub-articles (6) and (7) are added after sub-article (5) and the existing sub-article (7) is renumbered as sub-article (8):

"6/ Where an employee who has received retirement or invalidity gratuity pursuant to this Proclamation or Public Servants Pension Proclamation is re-employed as an employee of a private organization covered by the Private Organizations Employees Pension Scheme, his former service shall, without prejudice to sub-article (3) of Article 15 of this Proclamation, be counted along with the new service; provided that the gratuity is paid back.

7/ A person to whom reimbursement of pension contribution has been made pursuant to this Proclamation or the Public Servants Pension Proclamation before the coming in to force of this Proclamation, if employed as an employee of a private organization covered by the Private Organizations Employees Pension Scheme before retirement age, his former service shall, without prejudice to sub-article (3) of Article 15 of this Proclamation, be counted along with the new service; provided, however, that the reimbursed contribution he received shall be paid back with interest calculated at bank deposit interest rate."

5/ sub-article (1) of Article 18 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new sub-article (1):

"፩/ ቢያንስ ፲ ዓመት ያገለገለ የግል ድርጅት ሠራተኛ ይህ አዋጅ ከጸናበት ቀን አንስቶ አገልግሎት ካቋረጠ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፲፯ ንዑስ አንቀጽ(፩) ላይ በተደነገገው መሰረት የጡረታ መውጫ ዕድሜው ሲደርስ የአገልግሎት ጡረታ አበል እስከ ዕድሜ ልኩ ይከፈለዋል።"

፮/ የአዋጁ አንቀጽ ፲፰ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተሠርዞ ነባሮቹ ንዑስ አንቀጾች (፫) እና (፬) እንደቅደም ተከተላቸው ንዑስ አንቀጾች (፪) እና (፫) ሆነው ተሸጋሽገው ነባሩ ንዑስ አንቀጽ (፭) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፬) ተተክቷል፦

"፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)፣ (፪) ወይም (፫) መሰረት አገልግሎቱ የተቋረጠ የግል ድርጅት ሰራተኛ የጡረታ መውጫ ዕድሜው ሳይደርስ በጤና ጉድለት ምክንያት ለሥራ ብቁ አለመሆኑ ከተረጋገጠ ይኸው ከተረጋገጠበት ጊዜ ቀጥሎ ካለው ወር ጀምሮ የአገልግሎት ጡረታ አበል እስከ ዕድሜ ልኩ ይከፈለዋል። የሞተ እንደሆነም ከሞተበት ጊዜ ቀጥሎ ካለው ወር ጀምሮ ለተተኪዎች አበል ይከፈላል።"

፯/ በአዋጁ ከአንቀጽ ፲፱ ንዑስ አንቀጽ (፩) ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጾች (፪) እና (፫) ተጨምረው ነባሩ ንዑስ አንቀጽ (፪) ንዑስ አንቀጽ (፬) ሆኖ ተሸጋሽጓል፦

"፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ መዋቅራዊ አደረጃጀትና የተጠና የደመወዝ ስኬል

"1/ An employee of a private organization who has served for at least 10 years, if terminates his contract of employment after the coming into force of this Proclamation, he shall receive retirement pension benefit for life upon attaining retirement age as stipulated under sub-article (1) of Article 17 of this Proclamation."

6/ sub-article (2) of Article 18 of the Proclamation is deleted and the existing sub-articles (3) and (4) are renumbered as sub-articles (2) and (3), respectively, and the existing sub-article (5) is deleted and replaced by the following new sub-article (4):

"4/ Where it is ascertained that an employee of a private organization who has separated from service in accordance with sub-article (1), (2) or (3) of this Article due to health problems which prevents him from engaging in any remunerated work prior to attaining the retirement age, he shall receive retirement pension for life starting with the month following such ascertainment; in case he dies, his survivors shall be paid benefits starting with the month following his death."

7/ the following new sub-articles (2) and (3) are added after sub-article (1) of Article 19 of the Proclamation and the existing sub-article (2) is renumbered as sub-article (4):

"2/ Without prejudice to sub-article (1) of this Article, an employee who is employed in a private organization that

በሌለበት የግል ድርጅት አገልግሎ ወይም በሌላ ማናቸውም የግል ድርጅት ውስጥ በተቀጠረ በሦስት ዓመት ወይም ከዚያ ባነሰ ጊዜ ውስጥ በጡረታ የሚገለል ሠራተኛ በጡረታ ከሚገለልበት ወር ሦስት ዓመት አስቀድሞ ባለው ወር ሲከፈለው ከነበረው መደበኛ የወር ደመወዝ በ፳፭ በመቶ የሚበልጥ ዓመታዊ አማካይ የደመወዝ ጭማሪ ያገኘ እንደሆነ በየዓመቱ እስከ ፳፭ በመቶ ያለው የደመወዝ ጭማሪ ብቻ በደመወዙ ላይ ተደምሮ የሦስት ዓመት አማካይ የወር ደመወዙ ተይዞ ይታሰባል።

፫/ በመከላከያ ሠራዊት ወይም በፖሊስ አባልነት አገልግሎት ለፈጸመ ማንኛውም የግል ድርጅት ሠራተኛ ይኸው አገልግሎቱ በመንግስት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ለመከላከያ ሠራዊት እና ለፖሊስ አባል በተቀመጠው የስሌት ቀመር መሠረት ተሰልቶና ተዳምሮ ይታሰብለታል።"

፰/ የአዋጁ አንቀጽ ፳፩ ነባሩ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ (፩) ሆኖ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተጨምሯል፡-

"፪/ የግል ድርጅት ሠራተኛው በጡረታ ከተገለለበት ወር አንድ ዓመት አስቀድሞ ባለው ወር ሲከፈለው ከነበረው መደበኛ የወር ደመወዝ በማናቸውም ጊዜ ከ፳፭ በመቶ የሚበልጥ ዓመታዊ አማካይ የደመወዝ ጭማሪ ያገኘ እንደሆነ እስከ ፳፭ በመቶ ያለው አማካይ ዓመታዊ ደመወዝ ጭማሪ ብቻ በደመወዙ ላይ ተዳምሮ የዳረጎት አበሉ ይታሰባል።"

has no organizational structure or studied salary scale, or gets retired after serving for three years or lesser after his employment if paid more than 25% annual average salary increment on the salary paid a month before 3 years of his pension entitlement, the 25% annual average salary increment shall only be considered for the calculation of three years average monthly salary.

3/ For any private organization employee who has served as a member of the national defense force or as a member of police, the service shall be calculated and added in accordance with the formula set under Public Servant Pension Proclamation."

8/ the existing provision of Article 21 of the Proclamation shall be numbered as sub-article (1) and the following new sub-article (2) is added:

"2/ If a private organization employee gets more than 25% annual average salary increment at anytime on the normal salary paid a month before a year, the 25% annual average salary increment shall only be added for the calculatior of gratuity."

፱/ የአዋጁ አንቀጽ ፳፮ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፳፮ ተተክቷል፡-

"፳፮. የጡረታ መዋጮ ተመላሽ ስላለመደረጉ

የግል ድርጅት ሠራተኛው አገልግሎት በማንኛውም ምክንያት ቢቋረጥ ለግል ድርጅቱም ሆነ ለግል ድርጅት ሠራተኛው የጡረታ መዋጮ ተመላሽ አይደረግም።"

፲/ የአዋጁ አንቀጽ ፵፰ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተሰርዞ ነባሮቹ ንዑስ አንቀጾች (፫) እና (፬) ንዑስ አንቀጾች (፪) እና (፫) ሆነው ተሸጋሽገዋል፤

፲፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፶ ከንዑስ አንቀጽ (፪) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) ተጨምሯል፡-

"፫/ የአዋጅ ቁጥር ፮፻፺/፪ሺ፪ አንቀፅ ፱ እና የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ድንጋጌ ቢኖርም ለማህበራዊ ጤና መድህን የሚሰበሰብ የጤና መድህን መዋጮ በየወሩ ከጡረታ አበል ላይ ተቀንሶ ለጤና መድህን ፈንድ ገቢ ይደረጋል። ሆኖም፡-

ሀ) ወርሃዊ የጡረታ አበል በመቀበል ላይ ያለ ባለመብት በሠራተኛነት በመቀጠር ደመወዝ የሚያገኝ ከሆነ የጤና መድህን መዋጮ የሚቀነሰው በየወሩ ከሚከፈለው ደመወዝ ላይ ብቻ ነው፤

ለ) የጡረታ አበል በመቀበል ላይ ያለ ባለመብት የተተኪም ጡረታ አበል የሚያገኝ ከሆነ የጤና መድህን መዋጮ የሚቀነሰው በራሱ ከሚያገኘው ጡረታ አበል ላይ ብቻ ነው።"

9/ Article 26 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Article 26:

"26. **Non-Reimbursement of Pension Contribution**

If the employment contract of private organization employee is terminated due to any reason, the pension contribution may not be reimbursed for the private organization as well as for the private organization employee."

10/ sub-article (2) of Article 48 of the Proclamation is deleted and the existing sub-articles (3) and (4) are renumbered as sub-articles (2) and (3);

11/ the following new sub-article (3) is added after sub-article (2) of Article 50 of the Proclamation:

''3/ Notwithstanding the provision of Article 9 of Social Health Insurance Proclamation No. 690/2010 and sub article (1) and (2) of this Article, a contribution for social health insurance shall be deducted monthly from pension benefit and transferred to social health insurance fund. However:-

(a) if the beneficiary who receives monthly pension benefit also receives salary from employment, a contribution for social health insurance shall be deducted only from his monthly salary;

(b) if the beneficiary who receives pension benefit also receives survivors' pension benefit, the contribution for social health insurance shall be deducted only from the pension benefit he gets by his own.''

፲፪/የአዋጁ አንቀጽ ፶፩ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተተክቷል፦

"፩/ የጡረታ አበል በመቀበል ላይ ያለ ባለመብት በዚህ አዋጅ በሚሸፈን የግል ድርጅት ከተቀጠረና ለጡረታ መውጫ ዕድሜ ያልደረሰ ከሆነ አዲሱ አገልግሎት ከቀድሞ አገልግሎቱ ጋር ተደምሮ ይታሰብለታል:: ሆኖም እንደገና የታሰበው አበል ከቀድሞው አበል ያነሰ ከሆነ የቀድሞውን አበል የማግኘት መብቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ወደ ሥራ በመመለስ ለፈጸመው አገልግሎት የሚከፈለው አበል ወይም የጡረታ መዋጮ አይኖርም።"

፲፫/በአዋጁ አንቀጽ ፶፩ ከንዑስ አንቀጽ (፩) ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጾች (፪) እና (፫) ተጨምረው ነባሮቹ ንዑስ አንቀጾች (፪) እና (፫) ንዑስ አንቀጾች (፬) እና (፭) ሆነው ተሸጋሽገዋል፦

"፪/ በሁለት ወይም ከዚያ በላይ የግል ድርጅት ውስጥ በመቀጠር በሁለት ወይም ከዚያ በላይ የግል ድርጅት ደመወዝ ከሚከፈለው ሠራተኛ የጡረታ መዋጮ የሚሰበሰበው ሠራተኛው ከመረጠውና በአንድ የግል ድርጅት ከሚከፈለው ደመወዝ ላይ ብቻ ይሆናል፤ ሆኖም የግል ድርጅት ሠራተኛው የመንግስት ሠራተኛም ጭምር ከሆነ በግል ድርጅት ከሚከፈለው ደመወዝ ላይ የጡረታ መዋጮ አይሰበሰብም፤ አገልግሎቱም ለጡረታ አበል አወሳሰን አይታሰብም።

12/ sub-article (1) of Article 51 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new sub article (1):

"1/ If a private organization employee who receives pension benefit if employed in a private organization covered by this Proclamation and has not reached the retirement age, his new service shall be added to his previous service; provided, however, that if the retirement benefit based on the accumulated service is less than the previous one, without prejudice to his right to receive the previous pension, he may not receive any payment or contribution re-imbursement for the new service he provided."

13/ sub-articles (2) and (3) are added after sub-article (1) of Article 51 of the Proclamation and the existing sub-articles (2) and (3) are renumbered as sub-articles (4) and (5):

"2/ If a private organization employee is employed and salaried from two or more private organizations, the pension contribution may be collected according to his choice from salary paid by one private organization; provided, however, that if a private organization employee is a public servant as well, the pension contribution may not be collected from a salary paid by any private organization, and the service may not be calculated for pension benefit.

፫/ በዚህ አዋጅ ወይም በመንግስት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ መሠረት መጦሪያ ዕድሜ ፷ ላይ ከመድረሱ አስቀድሞ የአገልግሎት ጡረታ አበል የተወሰነለት ባለመብት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት እንደገና በመቀጠር የፈጸመው አገልግሎት ከቀድሞ አገልግሎቱ ጋር ተደምሮ አበሉ ተሻሽሎ የሚከፈለው መጦሪያ ዕድሜው ፷ ላይ ሲደርስ ብቻ ይሆናል፤ ሆኖም በሥራ ላይ ጉዳት ወይም በጤና ጉድለት ምክንያት ሠራተኛው ደመወዝ የሚያስገኝ ማናቸውንም ሥራ መሥራት የማይችል መሆኑ በህክምና ቦርድ ተረጋግጦ ከሥራ ሲሰናበት ከሥራ ከተሰናበተበት ወር ቀጥሎ ካለው ወር ጀምሮ አበሉ ተሻሽሎ ይከፈላል።"

፫. **<u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ ከሐምሌ ፩ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፫ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

3/ If a re-employed beneficiary was entitled to a retirement pension benefit pursuant to this Proclamation or Public Servant Pension Proclamation before the retirement age of 60, the new service that has been rendered by him shall be added to his pension benefit with the pervious service in accordance with sub-article (1) of this Article only when he attains the retirement age of 60; provided, however, that if it is ascertained by a medical board that the employee of a private organization is incapable of fulfilling service due to employment injury or health problems and separated from service, his pension shall be re-considered starting from the next month following his separation from service."

3. **<u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force as of the 8th day of July, 2015.

**Done at Addis Ababa, this 10th day of July, 2015.**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**